የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ–የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 19
ADDIS ABABA - 20th Feb., 1998

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፰/፲፱፻፺ ዓ.ም.
የሻይ ምርትና ገበያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ...................... ገጽ ፮፻፹፭

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 28/1998
Tea Production and Marketing Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations ... Page 685

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፰/፲፱፻፺

### የሻይ ምርትና ገበያ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>
ይህ ደንብ "የሻይ ምርትና ገበያ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፳፰/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>መቋቋም</u>
፩· የሻይ ምርትና ገበያ ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 28/1998

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE TEA PRODUCTION AND MARKETING ENTERPRISE

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*
These Regulations may be cited as the "Tea Production and Marketing Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No. 28/1998."

2. *Establishment*
1) There is hereby established the Tea Production and Marketing Enterprise (hereinafter 'the Enterprise') as a public enterprise.

፪· ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ።

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ።

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ይሆናል ። እንደአስፈላጊነቱም በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ።

፭· ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፡

፩· ሻይ ቅጠልን በፋብሪካ ማዘጋጀት ፤

፪· በፋብሪካ የተዘጋጀ ሻይ ቅጠልን ለገበያ ማቅረብ ፤

፫· ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ ።

፮· ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፳፪ ሚሊዮን ፱፻፳፰ሺ (ሃያ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃያ ስምንት ሺህ ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፲፩ ሚሊዮን ፬፻፷፫ሺ ፮፻፹፮ (አሥራ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ስልሳ ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል ።

፯· ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ።

፰· ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ።

፱· ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ፣ የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Enterprise is established are:

1) to engage in the processing of tea;
2) to engage in the marketing of processed tea;
3) to engage in any other related activities conducive to the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized Capital of the Enterprise is Birr 22.928,000 (twenty two million nine hundred twenty eight thousand Birr) of which Birr 11,463,686 (eleven million four hundred sixty three thousand six hundred eighty six Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be held liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 20th day of February, 1998.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE